# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች

# የጠፋው ልጅ



ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: Alastair Paterson; Lazarus
ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው):
Ruth Klassen; Sarah S.
የተተረጎመው: Abel Eshetu
አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

BFC
PO Box 3
Winnipeg, MB R3C 2G1
Canada

©2020 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።



ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር ምህረት ለሰዎች ይናገር ነበር። የአይሁድ መሪዎች ግን ከኃጢአተኞች ጋር ወዳጅ ስለነበር ኢየሱስን ይነቅፉት ነበር።

የመጀመሪያው ታሪክ መቶ
በጎች ስለነበሩት አንድ
ሰው ነበር። ከእነርሱም
አንዲቷ ጠፋችበት። ሰውዬው ወዲያው ዘጠና
ዘጠኙን ትቶ አንዲቷን ፍለጋ ሄደ።





እስኪያገኛትም ድረስ
በየቦታው ፈለጋት።
ሲያገኛትም ደስ
አለውና በትከሻው
ላይ ተሸክሟት ወደ
ቤቱ መጣ። ከዚያም
ለጎረቤቶቹ “ከእኔ
ጋር ደስ ይበላችሁ።

የጠፋችብኝን በግ
አግኝቻታለሁ”
አላቸው።

ኢየሱስም ንስሐ
በሚገባ በአንድ ሰው
በመንግስተ ሰማያት
ታላቅ ደስታ ይሆናል
አላቸው። ንስሐ ማለት
በኃጢአታችን በማዘን
ኃጢአትን ለመተው
ፈቃደኛ መሆን
ማለት ነው።





ኢየሱስ የነገራቸው
ሁለተኛው ታሪክ ደግሞ
አስር ድሪም (የብር
ሳንቲሞች) ስለነበራት
ሴት ነበር። ብዙ ጊዜ
ቆጥባ ያጠራቀመችው
ሊሆን ይችላል።
ያሳዝናል! አንዲቷ
ድሪም ጠፋችባት።

የጠፋባትን እስክታገኝ ድረስ ቤቷን ጠረገችው፣በረበረችው። ባገኘችውም ጊዜ ጐረቤቶችዋን ሁሉ ጠርታ የጠፋውን ድሪሜን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ አለቻቸው።





ኢየሱስም ንስሐ
በሚገባ በአንድ
ኃጢአተኛ
በእግዚአብሔር
መላእክት ፊት
ደስታ ይሆናል።

ኢየሱስ የነገራቸው ሶስተኛው ታሪክ
በጣም ያሳዝናል። የአባቱን ቤት ትቶ
ስለጠፋው ልጅ ነበር።



ልጁም ገንዘቡን ሁሉ ሰብስቦ ወደ ሩቅ አገር ሄደ፥ ከዚያም እያባከነ ገንዘቡን በተነ። ከዚያም በአገሩ ረሀብ ስለገባ በምግብ እጦት ይጨነቅ ጀመር።



ከረሀቡም የተነሳ የአሳማ እረኛ ሆነ። አሳማዎችም ከሚበሉት ምግብ ሊጠግብ ይመኝ ነበር፥ የሚሰጠውም አልነበረም። ወደ ልቡም ተመልሶ እንዲህ አለ፡ እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ አሽከሮች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በራብ እጠፋለሁ።





“ተነሥቼም ወደ አባቴ
እሄዳለሁና። አባቴ ሆይ፥
በሰማይና በፊትህ
በደልሁ። ወደ ፊትም
ልጅህ ልባል አይገባኝም።
ከአሽከሮችህ እንደ
አንዱ አድርገኝ
እለዋለሁ” አለ።

ተነሥቶም ወደ አባቱ መጣ። እርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት፥ አባቱም ወደ ልጁ ሮጦ አንገቱን አቀፈውና ሳመው።





ልጁም። አባቴ ሆይ፥
በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥
ወደ ፊትም ልጅህ ልባል
አይገባኝም አለው። አባቱ
ግን አሽከሮቹን አለ።
ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ
ልብስ አምጡና
አልብሱት፥ ለእጁ ቀለበት
ለእግሩም ጫማ ስጡ፤

ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና አሁን ሕያው ነው፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም። ደስም ይላቸው ጀመር። እግዚአብሔር በንስሐ ወደ እርሱ የሚመለሱትን ይወዳቸዋል።



# የጠፋው ልጅ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ሉቃስ ምዕ. 15

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16